# VPAS

የቪክቶሪያ
የወሊድ ጊዜ
የአስከሬን ምርመራ
አገልግሎት

# የልጅዎ የድህረ ሞት ምርመራ

ልጅዎ ማጣትዎ በጣም አዝነናል።

ይህ የመረጃ ወረቀት የተሰጠዎት የልጅዎን የድህረ ሞት ምርመራ እንዲካሄድ ስለተስማሙ ነው።

ይህ ምርመራ ልጅዎ የሞተበትን ምክንያት በተቻለን መጠን ለማወቅ ይረዳናል።

የእርስዎ የጤና ጥበቃ ቡድን ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ የሚያስችሉ ያለዎትን አማራጮች ይወያያል።

በተጨማሪም ልጅዎ የድህረ ሞት ምርመራ ማድረግ ይኖርበት እንደሆነና እንደሌለበት መወሰንን ጨምሮ በጽሁፍ የሰፈሩ ሌሎች መረጃዎችም ሊሰጥዎት ይገባ ነበር።

ይህ ካልሆነ፣ አንድ ቅጂ እንዲኖርዎት መጠየቅ ይችላሉ። ወይም ደግሞ በዚህ የመረጃ ወረቀት መጨረሻ ላይ ያለውን QR ኮድ ስካን በማድረግ ማንበብ ይችላሉ።

ይህ የመረጃ ወረቀት በሚቀጥለው ምን እንደሆነ፣ ምርመራው የት እንደሚካሄድና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከማን ጋር እንደሚገናኙ ያብራራል።

## ለድህረ ሞት ምርመራው ከተስማሙ በኋላ ምን ይደረጋል?

ከልጅዎ ጋር የተወሰነ ጊዜ ካሳለፉ በኋላ፣ የጤና ጥበቃ ቡድንዎ፣ የቪክቶሪያን የቅድመ ወሊድ/ፔሪናታል የአስከሬን ምርመራ አገልግሎት (VPAS) አስተባባሪ ልጅዎ ለድህረ ምርመራ ዝግጁ መሆኑን እንዲያውቅ ያደርጋል። የVPAS አስተባባሪ የልጅዎን ለምርመራ ወደ ልዩ ባለሙያ/ስፔሻሊስት ቦታ እንዲላክ ያዘጋጃል።

ልጅዎ ከእርስዎ እንክብካቤ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ የVPAS አስተባባሪውን ማነጋገር ይችላሉ። ለጥያቄዎችዎ መልስ ለመስጠት እና የፈለጉትን ያህል መረጃ እንዲነገርዎ ለማድረግ እዚያ ይገኛሉ። የእነሱን ዝርዝር መረጃዎች በዚህ የመረጃ ወረቀት መጨረሻ ላይ ያገኙታል።

## የድህረ ሞት ምርመራው የሚከናወነው የት ነው?

የልጅዎ የድህረ ሞት ምርመራ የሚካሄድበት ቦታ:

- ☐ Royal Women’s Hospital, Parkville (በሮያል የሴቶች ሆስፒታል፤ ፓርክቪል) Royal Children’s Hospital Pathology) (ሮያል ህጻናት ሆስፒታል ፓቶሎጂ)/
- ☐ Monash Health, Clayton (ሞናሽ ጤናጥበቃ፤ ክላይተን) (Monash Pathology) (ሞናሽ ፓቶሎጂ)
- ☐ Mercy Hospital for Women, Heidelberg (Austin Pathology) (መርስይ የሴቶች ሆስፒታል፣ ሃይደልበርግ/ (አውስቲንፓቶሎጂ)

## የድህረ ሞት ምርመራው ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?

የድህረ ሞት ምርመራው የሚጀምረው እንደ ራጂ/ኤክስሬይ ወይም ኤምአርአይ (MRI) ባሉ የውጫዊ ምርመራዎች ነው። እነዚህ ምርመራዎች በተቻለ ፍጥነት ይደረጋሉ፣ ግን እነዚህ አገልግሎቶች በሚገኙበት ጊዜ በመመስረት ጥቂት ቀናት ሊወስድ ይችላል።

እነዚህ ምርመራዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ውስጣዊ ምርመራው (የቀዶ ጥገና ሂደት) ማድረግ ይቻላል። ውስጣዊ ምርመራ ሶስት ሰዓት ገደማ ይፈጃል።

ይህ ለልጅዎ የቀብር ሥነ ሥርዓት ባለው እቅድ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል፣ ልጅዎ በእኛ እንክብካቤ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ማወቅ ለርስዎ አስፈላጊ እንደሆነ ይገባናል።

ልጅዎ በልዩ ባለሙያ/ ስፔሻሊስት ቦታ ላይ ከደረሰ በኋላ፣ መቼ ወደ እርስዎ እንደሚመለስ የ VPAS አስተባባሪ ይበልጥ ትክክለኛ የሆነ ሀሳብ ሊሰጥዎ ይችላል።

## ከድህረ ሞት ምርመራ በኋላ ምን ይደረጋል?

የድህረ ሞት ምርመራውን ስናጠናቅቅ፣ ከቀብር ሥነ ሥርዓት ዳይሬክተር ጋር በመሆን ልጅዎን ከእኛ እንክብካቤ ወደ እነሱ በደህና እና በአክብሮት ለማስተላለፍ ኣብረን እንሰራለን።

## ከድህረ ሞት ምርመራ በኋላ ልጅዎን ማየት ይችላሉን?

አዎ፤ አንዳንድ ወላጆች የድረ ሞት ምርመራው ከተከናወነ በኋላ ከልጃቸው ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ይመርጣሉ፣ ልጃቸው በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ዳረክተር እንክብካቤ ስር ሆኖ አሊያም አንዳንድ ጊዜ ቤት ውስጥ ነው።

ይህ ለቤተሰብዎ የግል ውሳኔ ነው።

ልጅዎ የሙሉ ወይ የከፊል የድህረ ሞት ከተደረገላቸው፣ የፐሪናታል ፓቶሎጂስት (ዶክተር) ቲሹዎቻቸውና ኣካሎቻቸውን ለመመርመር የቀዶ ጥገና ክፍተቶች (ኢንሲዥን) ያደርጋሉ። ከምርመራው በኋላ እነዚህን ክፍተቶች በጥንቃቄ ይዘጓቿል። ልጅዎ ከለበሰ በኋላ፣ ክፍተቶቹ ኣይታዩም።።

## የድህረ ሞት የምርመራ ውጤት የሚያገኙት መቼ ነው?

የድህረ ሞት ምርመራው ከተካሄደ በኋላ፣ የወሊድ ባለሙያ ፓቶሎጂስት ያገኙትን ውጢት የሚያብራራ ዝርዝር ዘገባ ይጽፋል። አብዛኛውን ጊዜ ሪፖርቱ ከ10 እስከ 12 ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል፤ በሚያስፈልጉት ምርመራዎችና ውጤቱን ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል በሚለው ይወሰናል። ሪፖርቱ እርስዎንና ልጅዎን ወደ ተንከባከበዉ ሀኪም ይላካል።

በልጅዎ የድህረ ሞት ምርመራ ስለተገኘው ለመወያየት ከእርስዎ ጋር ተከታዩን ቀጠሮ ይይዛሉ።

## የሐዘን ድጋፍ እና መረጃ

ተጨማሪ መረጃና ድጋፍ የሚያስፈልግዎ ከሆነ እባክዎ የጤና ጥበቃ ቡድንዎን ያነጋግሩ።

ስለነዚህ መረጃ ለማግኘት እነዚህን qr ኮዶች ስካን ማድረግ ይችላሉ፡

**በሐዘን ጊዜ የሚጠቅሙ መረጃዎች**

**የVPAS የቤተሰብ መረጃ**

## ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልግዎ ከሆነ የVPAS አስተባባሪን ያነጋግሩ

**T** 1800 841 024

**E** VPAC@thewomens.org.au

**ሰዓታት**

ከሰኞ እስከ ዓርብ

ከጥዋቱ 9:00am እስከ ከሰዓት በኋላ 5:00pm።